# መብቶችዎን ይወቁ

VOTE 2022

***እንደ ኣንድ የሚኖሶታ ድምጽ ሰጪ ኣያሌ መብቶች ኣሎት- እወቁዋቸው!***

## *ለመምረጥ ከስራ ፍቃድ ማግኘት*

ከደሞዝዎ ተቆራጭ ሳይደረግ፡ ካሎት የግል ፍቃድም ሆነ ከዓመታዊ እረፍቶ ሳይቆረጥ፡ ሂደው ለመምረጥ ፍቃድ ማግኘት መብትዎ ነው።

## *(እንደ ኢትዮጵያ ኣቆጣጠር) እስከ ምሽቱ 2 ሰዓት ድረስ ሰልፍ ላይ ከሆኑ መምረጥ ይችላሉ።*

እንደ ኢትዮጵያ ኣቆጣጠር ከምሽቱ 2 ሰዓት ድረስ ሰልፍ ላይ ከሆኑ (በፈረንጆች ኣቆጣጠር 8 P.M) የመምረጥ መብትዎ የተጠበቀ ነው።

## *በምርጫው ዕለት መመዝገብ*

የት እንደሚኖሩ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከያዙ፡ በምርጫው ዕለት ተመዝግበው የመምረጥ መብት ኣሎት።

## *በቃልዎ መፈረም*

ራስዎ ፊርማዎን መፈረም ካልቻሉ፡ ማን መሆንዎን በቃልዎ ኣረጋግጠው ሌላ ሰው እንዲፈርምልዎ የማድረግ መብት ኣሎት።

## *እርዳታ መጠየቅ*

ከአሰሪዎ ተወካይ ወይም ከማህበሮ ወኪል በስተቀረ፤ ከሌላ ከማንኛውም ሰው እርዳታ መጠየቅ ይችላሉ።

## *ወደ ምርጫው ጣብያ ልጆችን ማምጣት*

ልጆችዎን ከእርስዎ ጋር ወደ ምርጫው ጣብያ ማምጣት መብትዎ ነው።

### *የ2022 ቀናት*

*የማጣርያ ምርጫ*
*ማክሰኞ፡ ነሃሴ 9 ቀን*

*በኣካል ሳይገኙ የሚደረግ ምርጫ*
*በፖስታ መምረጥ ወይም በኣካል ተገኝተው የሚመረጥበት ቀን - ከመስከረም 23ቀን እስከ ህዳር 7 ቀን*

*ለመምረጥ ተመዝገቡ*
*በዋናው ምርጫ ቀን፡ ግዜ ለመቆጠብ ቀደም ብለው በግዜ እስከ ጥቅምት 18 ቀን ለመምረጥ ይመዝገቡ።*

*የምርጫ ቀን*
*ማክሰኞ ህዳር 8 ቀን*

*ከበስተጀርባ ይቀጥላል...*



# መብቶችዎን ይወቁ

VOTE 2022

*...ከበፊቱ ገጽ የቀጠለ*

## *የተፈረደቦትን የወንጀል ቅጣት ከፈጸሙ በውሃላ ምረጡ*

ወንጀል ፈጽመው የተበየነቦትን የቅጣት ግዜ(ከእስር ቤት ለግዜው መለቀቅን፡ ወይም ሌሎች ሁኔታዎችን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ጭምር ሙሉ በሙሉ ካጠናቀቁ በውሃላ) ለመምረጥ ይችላሉ።

## *በሰው ጥበቃ ስር እያሉ መምረጥ*

በሰው ጥበቃ ስር እያሉም፡ የመምረጥ መብትዎ በዳኛ እስካልታገደ ድረስ፡ የመምረጥ መብት ኣሎት።

## *በሌላ ሰው የማሳመን ተጽእኖ ሳይደረግቦ መምረጥ*

በምርጫው ጣብያ ውስጥ ማንም ሰው ምርጫዎን ለማስቀየር ጫና ሳያደርግቦ የመምረጥ መብት ኣሎት።

## *ሌላ ቅያር የምርጫ ወረቀት ማግኘት*

የምርጫ ሳጥን ውስጥ የመረጡትን ሰው ስም ከማስገባትዎ በፊት ተሳስቸለሁና ሌላ ኣዲስ ቅያር የምርጫ ወረቀት ስጡኝ የማለትና የማግኘት መብት ኣሎት

## *ቅሬታ መግለጽ*

የምርጫውን ኣካሄድ በሚመለከት ኣንዳች ቅሬታ ቢኖሮት፡ በኣክባቢዎ ላለው ኣስመራጭ ኮሚቴ ቅሬታዎን በጽሁፍ የማስመዝገብ መብት ኣሎት።

## *ለዓይነት የሚሆንዎ የምርጫ ወረቀት ወደ ምርጫው ቦታ ማምጣት*

ለዓይነት የሚሆንዎ የምርጫ ወረቀት ወደ ምርጫው ቦታ የማምጣት መብት ኣሎት።

## *የመራጮችን መብቶች ያለበትን ህጋዊ ወረቀት ማምጣት*

የመራጮች መብቶች በዝርዝር ያለበትን ህጋዊ ወረቀት ወደ ምርጫው ቦታ የማምጣት መብት ኣሎት።

*የሚኖሶታ የኣገር ውስጥ ኣስተዳደር ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት*
mnvotes.gov • 1-877-600-VOTE